የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

፴፩ኛ ዓመት ቁጥር ፶፪
አዲስ አበባ ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺ፲፯

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 52
ADDIS ABABA, 17th June, 2025

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፪/፪ሺ፲፯

የውሃ አካል ዳርቻ አስተዳደር አዋጅ ……..............................................ገጽ ፲፰ሺ፬፻፸፫

**Content**

Proclamation No. 1382/2025

Riparian Buffer Zone Management Proclamation……......…………..Page 18473

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፪/፪ሺ፲፯**

**<u>የውሃ አካል ዳርቻ ርቀት አወሳሰን፣ ልማት እና እንክብካቤ ረቂቅ አዋጅ</u>**

የውሃ አካል ዳርቻዎች ተፈጥሯዊ ይዘት ወደ ሌላ መሬት አጠቃቀም በመቀየሩ ምክንያት ከመጠን ያለፈ ደለል፣ ንጥረ ነገር፣ ኬሚካል እና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮች ወደ ውሃ አካል በመግባት በውሃው መጠን፣ ጥራት፣ ብዝሃ ሕይወትና የስርዓተ ምህዳሩ አገልግሎት ላይ ችግር እየተከሰተ በመሆኑ፤

ይህን ችግር ማስወገድ የሚቻለው የውሃ አካል ዳርቻ ርቀትን ወስኖ መከለል፣ ማልማትና መንከባከብ ሲቻል በመሆኑ፤

የውሃ አካል ዳርቻ መከለልና በዘላቂነት ማልማትና መንከባከብ የውሃ ስነ-ምህዳር አግልግሎትን ከማሻሻል ባሻገር ለአካባቢው ማህበረሰብ ተጨማሪ ማህራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን የሚያስገኝ በመሆኑ፤

**PROCLAMATION 1382/2025**

**<u>RIPARIAN BUFFER ZONE DELIMITATION , DEVELOPMENT AND CONSERVATION DRAFT PROCLAMATION</u>**

**WHEREAS**, water quantity, quality, Biodiversity, and related ecosystem services are being adversely impacted by the entry of excess sediments, nutrients, chemicals, and other similar materials resulting from the conversion of a riparian buffer zone to other land uses;

**WHEREAS**, such adverse impacts on water bodies can only be addressed if a riparian buffer zone is delimited, developed and conserved;

**WHEREAS**, delimiting, sustainably developing and conserving, riparian buffer zones beyond improving the water ecosystem and its use gives the local community social and economic benefits;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በውሃ አካል ላይ እየተከሰተ ያለውን ተግዳሮት ለመግታትና ጠቀሜታውን በዘላቂነት ለማስቀጠል የውሃ አካል ዳርቻ ርቀትና አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት ወሳኝ ሚና ያለው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ ፶፭ (፪) (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የውሃ አካል ዳርቻ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፪/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

፩/ **"ሥርዓተ-ምህዳር"** ማለት በውሃና በውሃ አካል ዳርቻ ውስጥ ያሉ ማናቸውም ሕይወት ያላቸው ነገሮች ከራሳቸው ጋርም ሆነ ሕይወት ከሌላቸው ነገሮች እንዲሁም ከአካባቢያቸው ጋር የሚያደርጉትን ያልተቋረጠ ተፈጥሮአዊ መስተጋብር የሚያሳይ ስርዓት ነው፤

፪/ **"የውሃ አካል"** ማለት ወንዝ፣ ሐይቅ፣ ግድብ፣ ውሃ አዘል መሬት፣ ምንጭ ወይም የከርሰ ምድር ውሃን ያጠቃልላል፤

፫/ **"የውሃ ብዝሃ ሕይወት"** ማለት በውሃ አካሉና በዳርቻው የሚገኝ ህይወት ያለው ነገር ነው፤

**WHEREAS**, putting in place a system for delimiting a riparian buffer zone distance and use is essential for halting the hazard water bodies face and ensuring their sustainable use;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (2) (a) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## Part One

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Riparian Buffer Zone Management Proclamation No. 1382/2025."

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ **"Ecosystem"** means a system that represents the constant natural processes and bonds that exist in any living things among themselves or other non-living things, the natural function and interaction with each other and with other organisms;

2/ **"Water Body"** means rivers, lakes, dams, wetlands, springs, or groundwater;

3/ **"Biodiversity"** means all the different kinds of life in water bodies and their riparian buffer zone;

፬/ **"የውሃ አካል ዳርቻ"** ማለት በወንዝ ግራና ቀኝ፣ በሐይቅ፣ በግድብ፣ በውሃ አዘል መሬት፣ በምንጭ እንዲሁም በከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ ዙሪያ አግባብ ባለው አካል የሚከለል ቦታ ነው፤

፭/ **"ውሃ አዘል መሬት"** ማለት የተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ እርጥበታማ፣ ረግረጋማ፣ ውሃ ጠገብ፣ ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ውሃ የተኛበት ወይም የሚፈስበት ማንኛውም መሬት ነው፤

፮/ **"የቁጥጥር የውሃ አካል ዳርቻ"** ማለት ከመሬት አጠቃቀም ጋር በተያያዘ በጎርፍ ወይም በውሃ ስርገት አማካኝነት ደለል እና ሌሎች በካይ ነገሮች ወደ ውሃ አካል እንዳይገቡ ለማስቀረት ከጥብቅ የውሃ አካል ዳርቻ ድንበር አንስቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተዘረዘሩ ታሳቢዎችን መሰረት በማድረግ ርቀቱ ተወስኖ የተከለለ ቦታ ነው፤

፯/ **"ጥብቅ የውሃ አካል ዳርቻ"** ማለት በውሃ ስርገትም ሆነ በጎርፍ ምክንያት ከቁጥጥር የውሃ አካል ዳርቻ አልፈው ወደ የውሃ አካል ሊገቡ የሚችሉ በካይ ነገሮችን ማስቀረት እንዲቻል ከፍጹም ጥብቅ የውሃ አካል ዳርቻ ድንበር አንስቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተዘረዘሩ ታሳቢዎችን መሰረት በማድረግ ርቀቱ ተወስኖ የተከለለ ቦታ ነው፤

4/ **"Riparian Buffer Zone"** means an area adjacent to a river, lake, dam, wetland, spring, and ground-water well delimited by an appropriate body;

5/ **"Wetland"** means any marshy land whether natural or artificial, permanent or temporary, with water that is static or flowing;

6/ **"Controlled Riparian Buffer Zone"** means an area of land whose distance has been delimited starting from a restricted riparian buffer zone in accordance with Article 5 of this Proclamation with a view to prevent sediments and polluntants from entering into a water body through flood or infiltration as a result of land use;

7/ **"Restricted Riparian Buffer Zone"** means an area of land whose distance has been delimited starting from a very restricted riparian buffer zone in accordance with Article 5 of this Proclamation with a view to prevent sediments and polluntants from entering into a water body through flood or infiltration passing through a controlled riparian buffer zone;

፰/ **“ፍጹም ጥብቅ የውሃ አካል ዳርቻ”** ማለት የውሃ አካል ዳርቻው እና ብዝሀ ህይወቱ በዘላቂነት ተረጋግቶ እንዲጠበቅ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ የተዘረዘሩ ታሳቢዎችን መሰረት በማድረግ ርቀቱ ተወስኖ የተከለለ ቦታ ነው፤

8/ **“Very Restricted Riparian Buffer Zone”** means an area of land adjacent to a water body whose distance is delimited in accordance with Article 5 of this Proclmation with a view to protect the water body and its biodiversity sustainably;

፱/ **“የከርሰ ምድር ውሃ ጉድጓድ”** ማለት ውሃ አመንጪ ወይም አስተላላፊ ከርሰ ምድርን አካል በመዝለቅ የተቆፈረ የውሃ ጉድጓድ ነው፤

9/ **“Water Well”** means a deep well, drilled to penetrate and reach underground permeable beds containing or transmitting water;

፲/ **“ደረጃ”** ማለት ጅረቶች እርስበርሳቸው ሲገናኙ የሚፈጥሩት የፍሰት መጠን ለውጥ መግለጫ ነው፤

10/ **“Stream Orde**r**”** means a description of change of flow quantity / size created when streams join;

፲፩/ **“በካይ ንጥረ ነገር”** ማለት ወደ ማናቸውም የውሃ አካል ሲጨመር፣ ሲለቀቅ ወይም ሲገባ የውሃ አካሉን ብዝሃ ህይወትና ስርዓተ ምህዳር የሚጎዳ ጠጣር፣ ፈሳሽ ወይም ጋስ ነው፤

11/**“ Pollutant”** means any matter that can harm the biodiversity and ecosystem of a water body when introduced, discharged, or released directly or indirectly into it in any liquid, solid, or gaseous form;

፲፪/ **“ ነባር ልማት”** ማለት ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ልዩ ልዩ አገልግሎት እንዲሰጥ በዚህ አዋጅ ርቀቱ በተወሰነ የውሃ አካል ዳርቻ ውስጥ የተገነባ ወይም በመገንባት ላይ ያለ ማንኛውም ግንባታ ሲሆን የግብርና ስራን ይጨምራል፤

12/ **“Existing Development”**means any existing development constructed or under construction before the issuance of this Proclamation within the delimited riparian buffer zone according to this Proclamation for the purpose of undertaking various services including agricultural activity;

፲፫/ **"አግባብ ያለው አካል"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ እና ፲፰ መሠረት እንደቅደም ተከተሉ የፌደራል መንግሥት ሥልጣንና ተግባርን በተመለከተ ሚኒስቴሩ እንዲሁም የክልል ስልጣንና ተግባርን በተመለከተ በክልሉ መንግሥት ይህን አዋጅ እንዲያስፈፀም ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

፲፬/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ መስተዳደሮችን ይጨምራል፤

፲፭/ **"ከተማ"** ማለት በክልል መስተዳድር ምክር ቤት ማዘጋጃ ቤት ተቋቁሞለት ወይም የመሬት አስተዳደሩም በከተሞች መሬት አስተዳደር አዋጅ የሚመራ ከተማ ነው፤

፲፮/ **"ሚኒስቴር"** ማለት የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ነው፤

፲፯/ **"ሰው"** ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፰/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለፅ የሴት ጾታን ይጨምራል።

## ፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ በሚገኝ ማንኛውም የውሃ አካል እና የውሃ አካል ዳርቻ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

13/ **"Appropriate Body"** means according to Article 17 and 18 of this Proclamation respectively, regarding the powers and responsibilities of the Federal Government, the Ministry, and the power and responsibilities of Regional Governments, any organ assigned by the Regional Government to execute this proclamation;

14/ **"Regional State"** means any state established according to Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

15/ **"City"** means a city administered by the Municipal Council established by the regional state or its land administration governed by the Urban Land Administration Proclamation;

16/ **"Ministry"**means the Ministry of Water and Energy;

17/ **"Person"** means any natural or juridical person;

18/Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall apply to any water body and riparian buffer zone in the country.

## ክፍል ሁለት

**፬. የውሃ አካል ዳርቻ አከላለል**

፩/ የውሃ አካል ዳርቻ፡-

ሀ) የቁጥጥር፤

ለ) ጥብቅ፤ እና

ሐ) ፍጹም ጥብቅ፤

ተብሎ ይከለላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የውሃ አካል ዳርቻ ሲከለል የአከላል ወሰኑን የሚያሳይ አጥር ወይም ምልክት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ መሰረት አግባብ ባለው አካል ሊቀመጥ ይገባል።

**፭. የውሃ አካላት ዳርቻ ርቀት አወሳሰን**

፩/ የውሃ አካላት ዳርቻ ርቀት እንደ አግባብነቱ የሚከተሉትን ጉዳዮች ታሳቢ ያደረገ ይሆናል፡-

ሀ/ የውሃ አካላት አይነት ወይም ደረጃን፣

ለ/ በመቶ ዓመት ውስጥ የሚከሰት ከፍተኛ ጎርፍ የሚሸፍነው መሬት፣

ሐ/ የመሬት ተዳፋትነት፣

መ/ ተፈጥሯዊ የውሃ መገኛ ወይም ማበልጸጊያ ቦታ፣

ሠ/ የውሃ አካል ተፈጥሯዊ ድንበር፣

ረ/ ከተማ እና ገጠር፣

ሰ/ የመሬት አጠቃቀም፣

፪/ የውሃ አካላት ዳርቻ ርቀት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን ታሳቢዎች መሠረት በማደረግ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

## Part Two

**4. Delimitation of Riparian Buffer Zone**

1/ Riparian Buffer Zone shall be delimited as:

a) Controlled;

b) Restricted; and

c) Very Restricted;

2/ Where Riparian buffer zones delimited in accordance with Sub-Article (1) of this Article, a fence or sign shall be installed or marked to identify their boundary by the appropriate body based on a Directive to be issued for the implementation of this Proclamation.

**5. Riparian Buffer Zone Delimitation**

1/ Riparian buffer zone delimitation takes into account the following considerations as appropriate:

a) type water bodies'and stream order,

b) a maximum edge of 100 years floodplain,

c) land slope,

d) natural water sources or recharge areas,

e) natural boundary water bodies,

f) urban and rural,

g) land use,

2/ Delimitation of riparian buffer zone according to Sub Article (1) of this Article shall be determined by a Regulation to be issued by Council of Ministers.

## ክፍል ሶስት

### ፮. ስለተከለከለ ተግባር

፩/ በቁጥጥር የውሃ አካል ዳርቻ ውስጥ የሚከተለውን ተግባር ማከናወን የተከለከለ ነው፡-

ሀ) አደገኛ ወይም መርዛማ ኬሚካል መድፋት ፣ መልቀቅ ፣ መጣል፣ ማከማቸት ወይም መቅበር በተጨማሪም በዙሪያዉ መጠቀም የተከለከለ ነዉ፤

ለ) ደረቅ ወይም ፍሳሽ ቆሻሻ፣ መድፋት፣ መልቀቅ፣ማከማቸት ወይም መጣል፤

ሐ) ዓይነ ምድር መጸዳዳት፤

መ) የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ወይም የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ የሌለው ተቋም ግንባታ፤

ሠ) የፍሳሽ ማጣሪያ የሌለው የተሽከርካሪ እጥበት፤

ረ) ዛፍ መቁረጥ ወይም እጽዋት መመንጠር

ሰ) ልቅ ግጦሽ

፪/ በጥብቅ የውሃ አካል ዳርቻ ውስጥ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተከለከሉት ተግባራት በተጨማሪ የሚከተለውን ማከናወን የተከለከለ ነው፡-

ሀ) ከቋሚ የፍራፍሬ ተክል ልማት ውጭ የሆነ እርሻ፤

ለ) የመኖሪያ ቤት ግንባታ፤

ሐ) የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ወይም የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ካለው የቱሪዝም መዳረሻ ተቋም በስተቀር ማነኛውም ተቋም ግንባታ፤

መ) የውሃ አካል ብዝሀ ሕይወት ደህንነት ወይም የወንዝ የተፈጥሮ ፍሰት የሚያዛባ የማዕድን ማውጣት፤

## Part Three

### 6. Prohibited Activities

1/ It is prohibited to undertake the following activities within a controlled riparian buffer zone:

a) discharging, releasing, storing, dumping, or burying and using in the surrounding dangerous or poisonous chemicals;

b) discharging, releasing, dumping, or storing solid or liquid waste;

c) defecating;

d) building an entity that doesn't have a solid or liquid waste management system;

e) a car wash that doesn't have a liquid waste treatment system;

f) cutting trees and clearing vegetation; and

g) unrestricted grazing.

2/ In a restricted riparian buffer zone, in addition to those prohibited under Sub-Article 1 of this Article, it is prohibited to undertake the following activities:

a) any agricultural activity except fruit cultivation;

b) construction of residential house;

c) any construction except facilities for tourism with solid and liquid waste management and disposal systems;

d) a mining activity that changes the biodiversity of a water body or the natural course of a river;

ሠ) የቀብር ቦታ ማዘጋጀት፤

ረ) የተሽከርካሪ እጥበት።

፫/ በፍጹም ጥብቅ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ከተከለከለ ተግባር በተጨማሪ የሚከተለውን ማከናወን የተከለከለ ነው፡-

ሀ) እርሻ ወይም ከብት እርባታ፤

ለ) ከተፈቀደ መግቢያና መሸጋገርያ ግንባታ ውጪ የተሽከርካሪ መንገድ ስራ ወይም እንቅስቃሴ።

## ፯. የውሃ አካል ዳርቻ ልማትና እንክብካቤ

የውሃ አካል ዳርቻ ልማትና እንክብካቤ የአካባቢ ማህበረሰብን በሚያሳትፍ እና ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ አግባብ ባለው አካል ታቅዶ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

## ፰. ስለ ተቆጣጣሪ አካል

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት በተከለለ የውሃ አካል ዳርቻ ውስጥ የተከለከለ ድርጊት እንዳይፈጸም አግባብ ያለው አካል ተቆጣጣሪ ይመድባል፡፡

፪/ ተቆጣጣሪው አግባብ ባለው አካል በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በውሃ አካል ዳርቻ ውስጥ የዚህን አዋጅ አንቀፅ ፮ ድንጋጌን በመተላለፍ የሚፈፀም ድርጊትን ይቆጣጠራል፡፡

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቆጣጣሪው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

e) preparing a cemetery site;

f) car wash.

3/ In a very restricted riparian buffer zone, in addition to those prohibited under Sub-Article (1) and (2) of this Article, it is prohibited to undertake the following activities:

a) farming and cattle rearing; and

b) except for permitted walking trails and footbridges (overpass) construction, vehicle road construction, or movements.

## 7. Riparian Buffer Zone Development and Conservation

The development and conservation of riparian buffer zones shall be planned and implemented by the appropriate body in a manner that ensures the participation and benefit

## Part Four

## 8. Supervisory Body

1/ The appropriate body shall assign supervisors to control activities prohibited within a delimited riparian buffer zone under this Proclamation.

2/ Based on a Directive to be issued by the appropriate body, supervisors shall control any activity, within the delimited riparian buffer zone, that contravenes Article 6 of this Proclamation.

3/ Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the supervisor shall have the following powers and duties:

ሀ) የውሃ አካል ወይም የውሃ አካል ዳርቻን ሊበክል ይችላል ብሎ የጠረጠረውን የማንኛውንም ነገር የተመጠነ ናሙናን ለባለንብረቱ ወይም ለወኪሉ በጽሁፍ አሳውቆ የመውሰድ እና ጉዳት የሚያደርስ መሆን አለመሆኑን የመመርመር ወይም የማስመርመር፤

ለ) ጥፋት ተፈፅሞበታል ብሎ ወደጠረጠረው ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ በስራ ሰዓት የመግባት፤

ሐ) ይህን አዋጅ በመተላለፍ ጥፋት መፈፀሙን ለማስረዳት አካባቢውን ፎቶግራፍ የማንሳትና ተንቀሳቃሽ ምስል የመቅረፅ፤

መ) በተከለለ የውሃ አካል ዳርቻ ውስጥ በዚህ አዋጅ የተከለከለ ድርጊት ሲፈጸም ካገኘ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለሚመለከተው የጸጥታ አካል የማሳወቅ፤ እና

ሠ) ይህን አዋጅ ተላልፏል ተብሎ በሚጠረጠር ሰው ላይ ክስ ለመመስረት የሚያስችሉ መረጃዎችን አግባብ ላለው አካል የማስተላለፍ።

፬/ ተቆጣጣሪው ስራውን ሲያከናውን የደንብ ልብስ የመልበስና ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ የመያዝ ሲጠየቅም የማሳየት ግዴታ አለበት።

a) to take, upon notifying the property owner or its agent in writing, a sample from any material he suspected of causing pollution effect on the riparian buffer zone and to analyze or get it analyzed to ascertain whether it has an adverse effect or not;

b) to enter into a premise or compound, during working hours without prior notification or having a court order, wherein he suspects an offense to have been committed;

c) to take a sample, picture, or video of the surroundings in order to explain that an offense has been committed in violation of this Proclamation;

d) to notify the concerned law enforcement organ, to take appropriate measures regarding illegal activities being undertaken within the riparian buffer zone in violation of this proclamation; and

e) to hand over to the relevant body evidence necessary to initiate legal action against a suspect for violating this Proclamation.

4/ The supervisor shall wear a uniform, hold an identity card, and show it when requested.

**፱. <u>የሚኒስቴሩ ስልጣንና ተግባር</u>**

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚያስተሳስሩ ወይም ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የውሃ አካላት እንዲሁም በፌደራል መንግሥት በጀት የተገነቡ ግድቦችን ዳርቻ የመከለል፤

፪/ የውሃ አካል ዳርቻ አከላለል፣ ልማት እና እንክብካቤ የአተገባበር ማኑዋል ማዘጋጀትና የማሰራጨት፤

፫/ ውጤታማ እና ዘላቂ የሆነ የውሃ አካል ዳርቻ ልማት እና እንክብካቤ ተግባራት አፈጻጸም የክትትልና ግምገማ ስርዓት የመዘርጋት፤

፬/ አግባብነት ያላቸውን አካላት በማስተባበርና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህን አዋጅ የማስፈፀም፤ እና

፭/ በፌደራል መንግስት እና በክልል መንግስታት መካከል የውሃ አካላት ዳርቻዎች አከላለል፣ ልማት፣ አጠቃቀም እና እንክብካቤን የሚመለከት የመረጃ ልውውጥ ስርዓት የመዘርጋት፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

**፲. <u>የክልል መንግስት ስልጣንና ተግባር</u>**

የክልል መንግስት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖረዋል፦

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በሚኒስቴሩ የማይከለል የውሃ አካላት ዳርቻን የመከለል፤

**9. <u>Power and Duties of the Ministry</u>**

The Ministry shall have the following powers and duties:

1/ to delimit riparian buffer zones of water bodies that connect two or more regional states or are trans boundary, and dams built by the Federal Government budget;

2/ to prepare and distribute riparian buffer zone delimitation, development, and conservation manual;

3/ to set up a monitoring and evaluation system for implementing undertakings to ensure effective and sustainable development and conservation of riparian buffer zones;

4/ to implement this Proclamation by coordinating and providing technical support to stakeholders; and

5/ to set up an information exchange system between the Federal Government and Regional Governments regarding riparian buffer zones delimitation, development, use, and conservation.

## <u>Part Five</u>

**10. <u>Powers and Duties of Regional Government</u>**

Regional Government shall have the following powers and duties:

1/ to delimit riparian buffer zones of water bodies not to be delimited by the Ministry as per Sub-Article (1) of Article 10 of this Proclamation;

፪/ በፌደራልም ወይም በክልል መንግስት የተከለለ የውሃ አካል ዳርቻን የማልማት፣ የመንከባከብ፣ የመጠበቅ እና የመቆጣጠር፤

፫/ የተከለለ የውሃ አካል ዳርቻ ሕጋዊ ዕውቅና እንዲያገኝ የማድረግ፤

፬/ ለአካባቢው ማህበረሰብ ስለውሃ አካል ዳርቻዎች ልማትና ጥበቃ አስፈላጊነት እንዲሁም ጥቅም ግንዛቤ የመፍጠር፤

፭/ ግለሰቦች፣ ባለሀብቶች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትና የንግድ ድርጅቶች በውሃ አካል ዳርቻዎች ልማትና ጥበቃ ተግባር እንዲሳተፉ የማስተባበር፡፡

## ፲፩. <u>ስለ ነባር ልማት</u>

በተከለለ የውሃ አካል ዳርቻ ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ነባር ልማት ባለበት ሁኔታ ሊቀጥል የሚችለው በውሃ አካሉና ብዝሃ ህይወቱ ላይ ጉዳት ወይም ብክለት የማያስከትል መሆኑ አግባብ ባለው አካል ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

## ፲፪. <u>የመጠቆምና የመተባበር ግዴታ</u>

፩/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ የተከለከሉ ድርጊቶች በውሃ አካል ዳርቻ ውስጥ ሲፈፀም ወይም ለመፈፀም ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ካወቀ ለውሃ አካል ዳርቻ ተቆጣጣሪ ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ የሕግ አስፈጻሚ አካል የመጠቆም ግዴታ አለበት።

፪/ ማንኛውም ሰው ለውሃ አካል ዳርቻ ተቆጣጣሪ መረጃ የመስጠት፣ የቁጥጥር ተግባሩን ሲያከናውንም የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

2/ to develop, conserve, protect and control riparian buffer zones delimited by the Federal or Regional Government;

3/ to make the delimited riparian buffer zone get legal recognition;

4/ to raise the awareness of the local community on the importance of developing and conserving riparian buffer zones and their benefits; and

5/ to mobilize individuals, investors, governmental and non governmental organizations, and business entities to participate in developing and protecting riparian buffer zones.

## 11. <u>Riparian Buffer Zone Development and Conservation</u>

The development and conservation of riparian buffer zones shall be planned and implemented by the appropriate body in a manner that ensures the participation and benefit of the local community.

## 12. <u>Duty to Inform and Cooperate</u>

1/ Anyone, who is aware of the commission of or the preparation to commit acts that are prohibited under this Proclamation, is obliged to inform a riparian buffer zone supervisor or the nearest law enforcement body.

2/ Everyone is obliged to give information to and cooperate with a supervisor of a riparian buffer zone in carrying out his supervision duties.

**፲፫. <u>የወንጀል ቅጣት እና የአስተዳደር እርምጃ</u>**

፩/ ከዚህ አዋጅ አተገባበር ጋር በተያያዘ ለሚፈጸሙ ወንጀሎች በወንጀል ህጉ የተደነገጉ ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉ ግዴታዎችን አለመወጣት የሚያስከትለውን አስተዳደራዊ እርምጃ በተመለከተ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**13. <u>Criminal Sanction and Administrative Measures</u>**

1/ Criminal sanctions provided under the Criminal Code shall apply to crimes committed in relation to the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue a Directive specifying administrative measures against failure to discharge obligations imposed by this Proclamation.

**፲፬. <u>ስለተሻሩ ሕጎች</u>**

የውሃ ሀብት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፩፻፺፯/፩ሺ፱፻፺፪ አንቀጽ ፳፭ ድንጋጌ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

**14. <u>Repealed Laws</u>**

Article 25 of the Water Resource Management Proclamation No. 197/2000 is hereby repealed.

**፲፭. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**15. <u>Inapplicable laws</u>**

No laws or practices shall, in so far as they are inconsistent with this Proclamation.

**፲፮. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ደንብ ያወጣል፡፡

፪/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ እና አዋጁን ተከትሎ የሚወጣ ደንብ ለማስፈጸም የሚያስፈልግ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**16. <u>Power to Issue Regulations and Directives</u>**

1/ The Council of Ministers shall issue Regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ The Ministry may issue Directives necessary for the implementation of this Proclamation and the regulation.

፲፯. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ቀን ሰኔ ፲ ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀ ሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ**

**ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

17. **Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon its publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, On this 17th Day June of, 2025**

**TAYE ATSKE-SELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL**

**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**